ልብህን አስመልስ

ራስን በጥልቀት በመመልከትና ነገሮችን በማስተዋል ከሕይወት መሰናክሎችና ትብታቦች የመላቀቅ ምልከታ

በ ያስሚን ሙጃሂድ

ትርጉም
ሙሐመድ ሪሺድ
ስና
ሙሐመድ ሰዒድ

ነጃሺ ማተሚያ ቤት

የተርጓሚው ማስታወሻ

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይለናል ፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱدۡخُلُواْ فِي ٱلسِّلۡمِ كَآفَّةٗ وَلَا تَتَّبِعُواْ خُطُوَٰتِ ٱلشَّيۡطَٰنِۚ إِنَّهُۥ لَكُمۡ عَدُوّٞ مُّبِينٞ ﴾

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ሁላችሁም በመታዘዝ ውስጥ ግቡ። የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ፣ እርሱ ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነውና።» (አል-በቀራህ፡ 208)

ዛሬ ላይ የሰው ልጅ ሊጋፋው ከማይችለው ኃይል ጋር ተጋፍጧል። ከጦርነቱ፣ ከረሃቡ፣ ከስደቱ፣ ወዘተ. በላይ ከፊትለፊቱ የተደነቀረው ቴክኖሎጂ ነው ሕይወትን መቅኖ ያሳጣት። ቴክኖሎጂ ሕይወትን አስቸጋሪም ምቹም አድርጓታል። በርግጥ የማናውቀው እና የማንጋፋው ተዓምር የሆነ ኃይል ነው ቴክኖሎጂ።

ሕይወት ከቀን ወደ ቀን ከባድ ሆናለች።‹መብቃቃት› የምንለው ታላቁ ኢስላማዊ አስተምህሮ ከኡማው የሃሳብ ምኩራብ ወርዷል ብለን በድፍረት መናገር በምንችልበት ዘመን ላይ ነን። ስለ መብቃቃት ሳስብ ባጣሁ እና በነጣሁ ጊዜ ያለችኝን ጥሪት እንዳታልቅ እያጣጣርኩ እንዴት መጠቀም እንዳለብኝ የተቀመጠልኝ የከፉ ጊዜ መመሪያ ይመስለኝ ነበር። እያደግኩ እና በመጠኑም በሃሳብ እየሰፋሁ ስመጣ መብቃቃት በተትረፈረፈ ኑሮ ውስጥም ሊኖር እንደሚገባ ተገነዘብኩ። መትረፍረፍ ስል ብዙዎች የገንዘብን መትረፍረፍ ብቻ ሊያስቡ ይችላሉ። ሃሳቤ ግን ያ ብቻ አይደለም። የሃሳብ መትረፍረፍ፣ የምኞት መትረፍረፍ፣ የፍላጎት መትረፍረፍ፣ የጊዜ መትረፍረፍ፣ ወዘተ. ሕይወትን መቅኖ ከሚያሳጡ ነገሮች መካከል ናቸው። በነኚህ ነገሮች ውስጥ ሁሉ መብቃቃት ግድ ነው።

1- የሃሳብ መትረፍረፍ፡- በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የምናከማቻቸውን አእምሯዊ እውቀቶች፣ የተለያዩ መረጃዎች... በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ እየገቡ መሰናክል እንዳይሆኑ "በሃሳብ" መብቃቃት ውስጥ እንዴት መዘውተር እንደምንችል ማወቅና መተግበር አንደኛው ከችግር መውጫ መንገድ ነው። "ሰው ሃሳቡን ይመስላል" ይላሉና... የምናስበው ሃሳብ በራሱ በዚህ ሕይወት ውስጥ ለሚያጋጥሙን ችግሮች ሰበብ በመሆን ከፊት የሚሰለፍ ነው።

2- የምኞት መትረፍረፍ፡- ሰው እንደመሆናችን መጠን ብዙ ነገር እንመኛለን። ብዙ ነገር እንዲሆንልን እንተልማለን። ሆኖም በዚህ ሕይወት ውስጥ እየታደልነው የምንኖረው የተወሰነውን ብቻ ነው። አላህ ሱ.ወ. የፈቀደልንን ያህል ብቻ ነው የምናገኘው።

ነገር ግን ምኞት ገደብ የለውምና ብዙ እንዲሆንልን እንመኛለን።በምኞታችን ውስጥ መብቃቃትን ካላገኘን ባለን ነገር እንኳ ረከተን መኖር አይቻለንም።

3- የፍላጎት መትረፍረፍ፡- ይህ ከምኞት መትረፍረፍ የሚለየው ፍላጎት በየዕለቱ በሕይወታችን ውስጥ የሚከሰትብን በመሆኑ ነው። ምኞት በጊዜ ርዝመት ውስጥ ባብዛኛው የሚገለጥ ሲሆን፥ ፍላጎት ግን በቅፅበት ውስጥ የሚገለጥ ነው። መላው ዓለም ገበያ በሆነበት ዘመን ላይ ያለን በመሆኑ የፍላጎት መትረፍረፍ ወዴት ሊያደርሰን እንደሚችል መገመት ከባድ አይሆንም።

እነኚህ ከላይ የጠቀስኳቸውን እና ሌሎችን፡- መቆጣጠር ሰንችል፥ በዚያ አጋባሽነት፣ አከማችነት... ስፍራ በማጣት "በምንፈልገው" እና "በሚያስፈልገን" መሰረታዊ ነገር ላይ በማተኮር ኡማው ስላለበት ሁኔታ ማሰብና መጨነቅ እንደምንችል ነው።

እንደ ሰው ችግራችን ጥልቅ ነው። ብናውቀውም ባናውቀው ሁሌም መስቀለኛ መንገድ ላይ እንደቆምን ነን። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ፀሐፊዋ እንደጠቀሰችው የሙሳ ዐ.ሰ. ታሪክ ገላጫችን ነው። መላው ማኅበረሰብ ከባህሩ ፊትለፊት የቆመበት ሁኔታ ነው ያለው። እናም የርሳቸው ዓይነት በአላህ ሱ.ወ. የመተማመንን ስሜትና ከልብ ፅናት በመያዝ ነገሮችን መጋፈጥ ያስፈልገናል። አልያም እንደ ከፊሎቹ በማፈግፈግ የሚመጣብንን ፊትና በሽንፈት መወጣት ይኖርብናል። ለዚህ ሁሉ መጽሐፉ ምላሽ አለው።

አንዳንድ ሃሳቦች ተራ ይመስላሉ፤ ግና የሃሳብ ተራነት ያለው ወደተገቢው ቦታ በተገቢው መንገድ ባለመድረሱ ውስጥ መሆኑን በማመን ይህችን መጽሐፍ ለመተርጎም ተነሳሳሁ። እርግጥ ሃሳቡ የመጣው መተርጎም ከመፈለግ ጠንካራ ምኞት ውስጥ ሳይሆን በድንገቴ አሳብ ውስጥ ነው። ለማንበብ ስነሳ 'ለምን እየተረጎምኩ አላነበውም' የሚል ሀሳብ መጣልኝ፤ በይበልጥ ወደ መሃል ስደርስ ደግሞ ለምን በቁም ነገር ሃሳቡን አላበረታውም በማለት ለመጽሐፍ በሚሆን መልኩ ተርጉሜ ሰነድኩት።

መልካም ንባብ

ሙሐመድ ረሺድ

ረመዷን 1441 ዓ.ሂ.

ስለ መጽሐፉ እና ለፀሐፊዋ ከተሠጡ አስተያየቶች በጥቂቱ

ሕይወቴን ሙሉ በሙሉ ስለቀየርሽልኝ ላመሰግንሽ እወዳለሁ። አላህ ይባርክሽ።የጨለማ፣ የጭንቀት፣ የባዶነት እና የአሉታዊ ስሜት አስፈሪ ሕይወት ውስጥ ነበርኩ። አጋጣሚ ሆኖ የሆነ ጊዜ ካንቺ ጽሑፎች ጋር ተገናኘሁ። አሁን ደስ ብሎኛል። ሕይወቴ በርቷል። አልሐምዱሊላህ!። አላህ መልካሙን ሁሉ ያብዛልሽ። በመፃፍሽ ቀጥይ። አላህ ዱዓችንን ይቀበለን። እኔ ይሄንን የምለው ማለት ስላለብኝ ነገር ቃላት ስላጠረኝ ነው።

(መርየም ኢ.)

* * *

ቃላትሽ በጣም ልብ የሚነኩ ናቸው። ስለሆነም በማነብበት ጊዜ እያብላላሁ ቀስ እያልኩና ትንፋሽ እየሰበሰብኩ ነው። እኔ ሁሌም ቢሆን በማየው የማምን፣ ቁስ አምላኪ እና ራሴን ማስደሰትን በወደድኳቸው ሰዎች ላይ ጥገኛ ላለመሆን የምጥር ነኝ። ሰዎች ሲተዉኝ አሊያም ርቀውኝ ሲሄዱ እደነግጣለሁ፤ የምሆነው ይጠፋኛል። የመውደድ ፍላጎቴ ማብቂያ የለውም። በመውደዴም ደስታ አገኝበታለሁ። የዚህ መውደድ ምንጩ ከአላህ እንጂ ከሰዎች ጋር ካለኝ ግንኙነት ጋር መያያዝ የለበትም በሚል ሁሌም ትልቅ ጦርነት ውስጥ እንደገባሁ ነኝ። እኔ የሀሳብ ሰው ነኝ። እሠጣለሁ። ለሌሎች ደስታ መስጠት ደስታ ይሠጠኛል። ግና ከሰውም ሆነ ከዚህ ሕይወት ብዙ መጠበቅ እንደማይገባ መገንዘብና ማስታወስ ከባድ ነው። አልሐምዱ ሊላህ። ያንቺን ጽሑፍ ማንበቤ ወደራሴ እንድመለከት አድርጎኛል። ለዚህ ዓይነቱ ሀሳብ በርግጥ ዝግጁ አልነበርኩም። ግና አንቺን ማንበቤ ብዙ ረድቶኛል። እውነተኛ ስለሆንሽ አላህ ይባርክሽ።

(መሃር)

* * *

ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ጽሑፎችሽን እጅግ የወደድኩ መሆኔን ልገልጽሽ እፈልጋለሁ። ከስምንት ዓመቴ ጀምሮ አነብባለሁ። በተለይ ራስን በማነጽ ጉዳይ ላይ። ስለ ነፍስ የሚያወሩ እነ ሩሚን፣ ጋዛሊ እና ኢቅባልን እንዲሁም ሌሎች ብዙዎችን፡ : የብዙ ሰዎችን ድንቅ ሥራዎች ካነበብኩ በኋላ የራሴን ልብ እና ነፍስ በሥራዎችሽ ውስጥ ያገኘሁ መሆኔን ነው የምነግርሽ። ምርጫዬ ከሆኑ ፀሐፊዎች መካከል አንዱ ነሽ:: ራሴን ማስታወስ ስፈልግ ወደ ጽሑፎችሽ ነው የምሄደው። በሥራሽ አማካይነት በጣም የምወደውን ማግኘት ችያለሁ። ሥራሽ የነፍሴ ጓደኛ መሆኑን አስባለሁ። ለሱ ያለኝ ፍቅር ከሱ እንዳልርቅ አድርጎኛል። በሥራዎችሽ አማካይነት ነው ሕያው እና

ከያዙት ገመዱ የማይበጠሰውን አምላክ መውደድ የቻልኩት። እውነተኛ ፍቅር ምን እንደሆነ አስተምረሽኛል። ሥራሽን ወድጄዋለሁ። በጣም አነሳስተሽኛል። ወንድሜም ጭምር ሥራሽን ይወዳል፤ እንዲሁም ጓደኞቼ። አላህ ምርጥ የሆነውን ሁሉ እንዲሠጥሽና እንዲያፀናሽ፣ በበለጠ ሁኔታ ወደ አላህ ፍቅር የምታነሳሺን እንዲያረግሽ እለምነዋለሁ። ከታላቅ ፍቅር፣ አክብሮትና ዱዓ ጋር!

(ሙሕሲና -ደቡብ አፍሪካ)

* * *

"ያንቺ የዌብ ሳይትና የቪዲዮ መልዕክቶች እጅጉን ቀይረውኛል። ከዚያ በፊት ለነፍሴ ምግብ፣ ለልቤ ቀለብ የሚሆን ነገር ስፈልግላት ነበር። የዛን ልቤን የሚፈውስ ቀለብ። በዚሁ አጋጣሚ ነበር ያቺን ቪዲዮዎች ያገኘሁት። እህቴ ማሻአላህ ብያለሁ። ያንቺ ጽሑፍ ምን ያህል በነፍሴና በልቤ ላይ ተጽእኖ እንዳሳደረ ለመግለጽ ይከብደኛል። እያንዳንዱ የምትጽፊው ቃል ልብን የሚነካ፣ ነፍስን ቆስቁሶ እንባን ለማፍሰስ የሚዳርግ ነው። በሥራዎችሽ እና በተከታታይ ምክሮችሽ ለምታበረክቺልን አስተዋጽኦ ሁሉ እንዴት ማመስገን እንዳለብኝ አላውቅም። አላህ የላዕላዩን ጀነት ይስጥሽ። በዱንያና በአኺራ መልካሙን ሁሉ ይለግስሽ። አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ።

(ሙኒራ -ሲንጋፖር)

* * *

"ማሻአላህ! መልካምን ነገር ወደ አንድ ሰው ልብ ውስጥ እንዴት መግባት፣ ገብቶም መቀስቀስና መሥራት ያለበትን ነገር በምን መልኩ መሥራት እንዳለበት ታሳዩ ዘንድ አቅም ሠጥቶሻል። ያስሚንና መሰሎቿን የሠጠንን አላህ አመሰግናለሁ።"

(ጋዚ አ.)

* * *

"ማስመሰል የተሞላበት ሕይወት እኖር ነበር ብዬ አስባለሁ። በአንደበቴ አላህን እወዳለሁ ብልም ድርጊቴ ግን በተቃራኒው ነው። ድርጊቴ ያንደበቴን የሚያንፀባርቅ አይደለም። የሕይወት ለውጤ የጀመረው አላህን የማፍቀር እውነተኛ ምንነት ካንቺ ንግግሮችና ጽሑፎች ውስጥ መገንዘብ በጀመርኩበት ጊዜ ነበር። አልሐምዱ ሊላህ!! አሁን ሁሉም ነገር ቀጥተኛ መስመሩን እየያዘ ነው...!!"

(ናዚር)

* * *

"ያስሚን፤ እኔ በርግጥ አላውቅሽም። አንቺም እንደዚሁ። ነገር ግን ለኔ ቅርብ የሆንሽ ያህል ነው የሚሰማኝ! ሊያንዳንዱ የምትፅፊው መልዕክት በጥልቁ ውስጤን የሚነካኝ ነው- ይህንን አልሸሸግም።"

(ኑር)

* * *

"ተወኩል ከርማን አንቺን አስታወሰችኝ!! እሷ (ተወኩል) የውጫዊው ዓለም አብዮት ነፀብራቅ ስትሆን አንቺ ደግሞ የውስጣዊው ዓለም አብዮት ነፀብራቅ ነሽ።"

(ኤም. ኤ.)

* * *

"አላህ ጀነተል ፊርደውስን ይወፍቅሽ!! ምን ዓይነት መባረክ እንዳለሽ መግለፅ አልችልም ውድ እህቴ ያስሚን። አልሐምዱ ሊላህ... ያንቺን ጽሑፎች ማንበብ ከጀመርኩ ግዜ ጀምሮ በየቀኑ ኢማኔ እየጨመረና እየተስተካከለ ነው- አልሐምዱ ሊላህ። እንዲሁም ጽሑፎችሽን የማጋራቸው ጓደኞቼና የምወዳቸው ሌሎችም እንዲሁ ባንቺ ጽሑፍ ምክንያት ተነሳሽነታቸው ጨምሯል። አላህ ለዚህ ኡማ የመልካም ነገር ጠቋሚ መሳሪያ አድርጎ እንዲያሰማራሽ ያደረግሽውን ዱዓ ሰምቶሻል ማለት ነው።"

(ሃጀራ ኤም.)

* * * * * * * * * * * *

"እሱ ሊሰብራችሁ አይደለም። ላንድ ነገር እያዘጋጃችሁ ነው።
በነገሮች መካከል ስላሉ ልዩነቶች ግንዛቤን ሊሰጣችሁ ነው...
እናም ሕይወታችሁን ይቀይረዋል።"

ያስሚን ሙጃሂድ

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይለናል፡-

﴿ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْمَوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ﴾

«ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መኾኑን ሊሞክራችሁ፤ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው፤ እርሱም አሸናፊው መሓሪው ነው።» (አል-ሙልክ፡2)

* * * * * * * *